# ተመሰሳይና የተለመደ ድምፅ/ጩኸት እንቅልፍ አይከለክልም

ከታጋይካሕሳይ ቃሉ 01-21-17

በአለማችን የተለያየ የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም የሚወክሉ የተለያዩ አመለካከቶች ይታያሉ:: እነዚህ አመለካከቶች የተለያየ መልክና መገለጫ ቢኖራቸውም ከዲሞክራሲ አንፃር ግን ወይ ዲሞክራሲያዊ አልያም ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ናቸው:: በየትኛውም መለኪያ አንድ አመለካከት ሁለቱም ባህሪ ሊይዝ አይችልም::

በአገራችንም እየታዩ ያሉት አመለካከቶችም መልክና መገለጫው የትምክህት፤ የጠባብ እንዲሁም የዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ቢሆንም ባህሪያቸውና ይዘታቸው ግን ዞሮ ዞሮ በዲሞክራሲያዊና በፀረ- ዲሞክራሲያዊ በሌላ አነጋገር በልማታዊና በፀረ-ልማታዊ በአጠቃላይ ደግሞ በህዝባዊና በፀረ-ህዝብ ተብለው የሚመደቡ ናቸው:: በአሁኑ ግዜ በአገራችን በተለያየ አከባቢና መልክ እየታዩ ያሉትም መንስኤውና ምንጫቸው ከነዚህ አመለካከቶች የሚወጡ አይደሉም አልፎ አልፎ የሚታየው ግጭትና ሁከትም በመሀከላቸው ያለው የበላይነት ለመያዝ የሚደረግ ትግል ውጤት ነው::

ይህም በዋናነት በአንድ በኩል የትምክህትና የጥበት ሃይሎች በተናጠልም ሆነ ግምባር ፈጥረው በልላ በኩል ደግሞ የዲሞክራሲያዊ ብሄተኝነት ሃይሎች የህዝብ ውግንና ይዘው የሚያካሂዱት ትግል ጎልቶ እየታየ ነው:: የትምክህትና የጥበት ሃይሎች ምንም የሚያቀራርብ አስተሳሰብና አላማ ባይኖራቸውም በጣም የተጠናወታቸው የስልጣን ጥማት ምክንያት ባልበላውም ይደፋ አይነት የደሮ አስተሳሰብ ተባብረው ህዝብ ከህዝብ ጋር ሲያጋጩ ይታያል:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ከሰላም፤ ከህዝብ እድገትና መተባበር ተጠቃሚ እንዳይደሉ በሚገባ ስለሚያውቁ ነው::

የትምክህት ሃይሎች ከነሱ ወይም እንወክለዋለን ከሚሉት ማህረሰብ ውጪ ያለው የህብረተሰብ ክፍል የሁሉም ችግሮች ምንጭ ነው ብለው ያምናሉ፤ እንሱ ግን የተማሩ፤ ሁሉም ነገር እነሱ ቢሰሩት የተቃና፤ አለፍ ሲልም በፈጣሪ የታደሉ፤ የሁሉም ጥሩ የሚባል ታሪክና እሴት ፈጣሪዎችና ባለቤቶች አድርገው በመቁጠር የሰሩትም ያልሰሩትም ሰርቀውም ቢሆን ያወራሉ ያስወራሉ:: ይህን እውነት ለማስመስል ደግሞ መዋሸት፤ የሌላ ህዝብና ተወላጅ ማብጠልጠልና ጥላሸት መቀባት ደጋግመው ይሰሩበታል ዘርና ጎሳ በመቁጠር የሚተካከላቸው የለም:: በሌላ በኩል ጠባቦችም ቢሆን መነሻ ምክንያታቸው ተበድለናል የሚል ቢሆንም እነሱ በተራቸው እንደልባቸው የሚያደረጓት አገር ካልሆነ ደግሞ ብሄሬ የሚሉት አካባቢ በመነጠል ስልጣን ለመጨበጥ የሚያስቡ ናቸው በክፉ የበታችነት ስሜት ታውረው ይህን ፍላጎት ሊያስገኝልን ይችላል ከሚሉት ሰይጣንም ቢሆን ያብራሉ ምንም አይነት አይደሎጂና ግልፅ አላማም የላቸው ተሳክቶላቸው ስልጣን ቢይዙ እንኳ እንዴት እንደሚሄዱ አያውቁትም::

ሁለትም ግን የጋራ የሆነ ባህሪያትና መገለጫዎች አሉዋቸው ዋናው ነገር በህዝቦች መሀከል መተማመን እንዲፈጠር አይፈልጉም ለዚህም አንዱ ብሄር ከሌላው ብሄር ለማጋጨት አጥብቀው ይሰራሉ፤ ይህ የሚያደርጉት ደግሞ እየፈጠሩና እየዋሹ በዚህ አከባቢ የዚህኛው ብሄር እንደዚህ አደረገ፤ ተጨፈጨፈ የጨፈጨፈውም እገለ የሚባል ብሄር ነው፤ ያለቸው የህዝብ ንቀትም ያመሳስላቸዋል ይህም በተያየ መንገድ ይገልፁታል አንዱ ብሄር ከአንዱ የተሸለ እንደሆነ ሌላው አጥፊ እንደሆነ ስለሆነም ከሱ ጋር መወዳጀት እንደማያዋጣ ይሰብካሉ፤ ሌላው የሚያመሳስላቸው ደግሞ ሁለቱም አመለካከቶች ለሌላ ይቅርና እንወክለዋለን የሚሉት ህዝብም ቢሆን የማያምኑት መሆናቸው ነው፤ ከነሱ የተለየ ሃሳብ ከያዘ የተለያየ ስም በመስጠት ከገዛ ብሄሩ ለመነጠልና ለማግለል ይሰራሉ፤ የሃሳብ፤ የሃይማኖትና ሌሎች የብዝሃነት መገለጫ የሆኑ ልዩነቶች ለነሱ ስጋት ናቸው በመሆኑም አያስተናግዷቸውም:: ሰዎችን በሃይልና በማሸማቀቅ እንዲከተሉዋቸው ወይም ራሳቸው ደፍተው/አርፈው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ::

በሌላ በኩል የዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ሃይሎች ቀዳሚ እምነታቸው ሁሉም ሰዎች በብሄር፤ በሃይማኖት፤ በፖለቲካ፤ በአኗኗር፤ በባህልና በሚከተሉት አስተሳሰብ እኩል ናቸው በአገራቸውም የየራሳቸው ልዩነት ቢኖራቸውም አብረው ለመኖርና በጋራ ለማደግ

የሚያስችሉ የጋራ እሴት አሉዋቸው ብለው ያምናሉ:: የህዝቦች በጋራ ተፋቅረውና ተማምነው መኖር የእደገት ዋስትና መሆኑ በፅናት አምነው ይሰራሉ::

በመሆኑም አሁን በአገራችን እየታየ ያለው ጎራ ለይቶ የመታገል ሂደት በነዚህ አመለካከት መካከል የሚደረግ የሞት የሽረት ትግል መሆኑ ልብ ይለዋል::

ለመንደርደሪያነት ይህን ካልኩ ወደ ዋናውን መነሻ የሆነኝ ሃሳብ ልግባ:: መነሻየ የአቶ እውነቱ በተደጋጋሚ በትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ህወሓት ያነጣጠረ በጭፍን ጥላቻ የታጨቀ ውሸት የተሞላ ውንጀላቸው ነው:: አቶ እውነቱ ቀደም ሲል "በትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ያነጣጠረው የውሸት ውንጀላ እስከ መቼ" በሚል ለሰጠሁዋቸው ምላሽ ብለው "አውቆ የተኛን ተቀስቅሶ...እንዳይሆን ነገሩ" በሚል እኔ ከደሙ ንፁህ ነኝ የሚል መልእክት ያለው ሁሌ በሚሰድቧቸውና የውንጀላቸው ሰለባ በሆኑት በአይጋ ፎረምና ትግራይ ኦንላይን አውጥተዋል::

በሚገርም ነገር አሁንም ፅሁፋቸው የጀመሩት እነዚህ የፈረደባቸው ድረ-ገፆች በማሸማቀቅ ነው:: **"እኔ (አቶ እውነቱ) የምሰጣቸው ፅሁፍ አያወጡም ታጋይ ካህሳይ የሰጡዋቸው ግን ሶስቱም (ሆርንአፋየርን ጨምረው) ተቀባብለው አወጡ ለመሆኑ ታጋይ ካሕሳይ ተመሳሳይ ይዘትና ተደራሽ ላለው ፅሁፋቸው ምንም ለውጥ ሳያደርጉ በሶስት ድረ-ገፅ አወጡት"** ሲሉ ወቀሳቸው ጀመሩ ብልጥ ልጅ ይዞ ያለቅሳል እንደሚባለው ድረገፆቹ የእሳቸው እያወጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ እሳቸውም ተመሳሳይ ፅሁፍ ምንም ሳያደርጉበት በሁሉም ድረ-ገፆች አወጡት:: ለማኛውም ድረ-ገፆቹ የራሳቸው አላማና ፖሊሲ ያላቸው ናቸው በመሆኑም ማንኛውም ፀሃፊ ለሚፅፈው ጉዳይ ሃላፊነት የሚወስደው ራሱ ቢሆንም ከድረ-ገፆቹ አላማና ፖሊሲ ተስማምቶ መፃፍ አለበት:: ስለሆነም አቶ እውነቱ ፅፈውት ያልወጣ ካለ ችግሩ የሚሆነው እርስዎ ከድረ-ገፆች አላማና ፖሊሲ የወጣ ነው እንጂ ሌላ ምክንያት ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም በነዚህ ድረ-ገፆች እየተሰተናገዱ ስለሆነ:: ይህ ከሆነ ሃቁ ታድያ ምን ሆኑ ቢባል ነገሩ ወዲህ ነው አቶ እውነቱ የትግራይ ተወላጅና ህወሓት ጥላሸት መቀባት እንጂ ለሰራው ጥሩ ስራ መወደስ የለበትም ብለው ስለሚያምኑና ይህን እምነታቸው ያልተጋራ ፍጡር የትግራይ ተወላጅም ባይሆን ተለጣፊ ነው::

ትንሽ ወረድ ብለው ደግሞ የእሳቸው ፅሁፍ ታጋይ ካሕሳይን እንዳባሳጨና ከአንጀቱ እንደገባና ከሁለት አመት በፊት የፃፉት ፅሁፍ እስከመጥቀስ አስኬዳቸው ይሉናል:: ይህ እውነት አምነውበት ከሆነ ለፅሁፋቸው ከሰጡት ይጋጫል ምክንያቱም ፅሁፋቸው ቀስቅሶኛል ማለት ስለሆነም አልተሳካም:: እዚህም ውሸታቸው ይቀጥላል (ከ10 አመት በፊት ቢፅፉትም ለኔ ለውጥ ባይኖረም) የእሳቸው ፅሁፍ ግን የወጣው ጥር 2008 እኔ የፃፍኩት ደግሞ ታህሳስ 2009 ይህ እንዴት ከሁለት አመት በፊት ይባላል መዋሸትና ማጋነን ልምድ ካልሆነ በስተቀር:: ለነገሩ ጊዜው ምንም ለውጥ የለው እርስዎ እንዳሉት ከሁለት አመት በፊት ከሆነ የኢህደግ አመራር አባል ሆነው ኢህአደግን ውስጥ ውሰጡን መቦርቦር ከጀመሩ ቆይተዋል የሚል መልእክት ነው ያለው:: ሃቁ ግን እንዲቀሰቀስ የፈለጉት እኛን ከሆነ የተለመደ ጩኸት እንቅልፍ ስለማይከለክል ነው::

በጣም የሚገርመው በ1983 ኢህአፓ ተጋብዞ ነበር አልተጋዘም ያሉት ውሸት ነው ስላቸው በወቅቱ እሳቸው ከኔ እኩል ወይም በተሻለ እንደሚያውቁ ለዚህም ማስረጃቸው ከግንቦት 20 በፊት ኢሰፖ የሚሳተፍበት የሽግግር መንግስት እንዲመሰረት ኢህአደግ ሃሳብ አቅርቦ እንደነበር አሉኝ:: አጀንዳው ከደርግ ውድቀት በኋላ ስለሆነ እኮ ነው አሁን መደናገሩ ይቅርና ከደርግ ውድቀት በኋላ ከኢሰፖ በስተቀር ያልጋበዝ የለም ኢህአፖም ተጋብዘዋል እያልኩ ነው አዎ የሚሉ ከሆነ ለምን መዋሸት ፈለጉ አልተጋበዝም የሚሉ ከሆነ ማስረጃዎ ቢያቀርቡ

አቶ እውነቱ ይህን ካሉ በኋላ እኔ የሰጠሁዋቸው አስተያየት ማስተባበል ወይም ማብራራት ሲገባቸው አደበስብሰው ለማለፍ ነው የሞከሩት እንዲያውም አንዳንዱ እንደለመዱት **ድፍረት** ብለውታል አይሳካም እንጂ ማስፈራርያ መሆኑ (ይህም የትምክህት ሃይሎች የነሱ ሃሳብና እምነት የማይጋራን ለማሸማቀቅ የሚጠሙበት ስልት ነው) አዎ አንድ ነገር ላረጋግጥሎት እኔ በበኩሌ የመሰለኝና ያመንኩበትን ነገር አፌ ሞልቼ ለመናር በትግሌ ያገኘሁት እንጂ የተሰጠኝ እንዳልሆነ ነው::

ቀጥለውም ለትግራይ ህዝብ ከኔ (ታጋይ ካሕሳይ) ባልተናነሰ ከልብ የመነጨ ክብርና ሞገስ ያላቸው መሆኑ ሊነግሩኝ ሞክረዋል:: በህግ አምላክ የሚባለው ይህ ነው:: እንዴት ብሎ ነው ይህ የሆነው የአቶ እውነቱ በትግራይ ህዝብ ላይ እንዳላቸው አንዲት

ትንሽ ነገር ማሳየት ይችላሉ? እኔ ግን በትግራይ ህዝብ ያልዎትን ጭፍን ጥላቻ በብዛት ገልጬ ነበር እኮ እነሱን እኮ ማስተባበልና ማብራራት አልቻሉም:: በዚች ፅሁፎ እኳ ድረ-ገፆቹ ለማሽማቀቅ ሲሉ "ህወሓትንና የትግራይ ህዝብ የሚያሞግስና የሚከላከል" እንዲሁም "የትግራይ ህዝብና የህወሓት አስተዋፅኦ ከሚገባው በላይ" የሚሉት ሃሳበዎችዎ በሚገባ ሲገልፁ የትግራይ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ጎንደር ላይ በጠራራ ፀሃይ ሲዋረድ፤ ሲገደልና ሲባረር ግን እርስዎ እንደአመራር ሰላማዊ ሰልፋም ጥሩ እንደነበረና የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ እንደሆነ (የተያዘው መፈክርና ጠያቄ ግን ትግሬ ከአገራችን ይውጣ የሚል ነበር የተጠየቀውም ይህ) እንደ ብአዴን አመራር በተደጋጋሚ ከመናገርዎ በተጨማሪ የደረሰው ጉዳት ያሳዘናቸው መሆኑ የገለፁት ነባር የብአዴን ታጋዮች የህወሓት ተለጣፊ ብለው በግልፅ ስም ጠቅሰው አልፃፉም እንዴ? ሌላስ እያንዳንዱ በትግራይ ተወላጅ የተሰራው ስራ ብቻ ሳይሆን ያልሰራው በፈጠራ ወሬ ይህ ይትግራይ ተወላጅ ስራ ነው እያሉ አይደለም እንዴ ለምሳሌ የስድስተኛ ክፍል መፅሃፍ በተመለከተ፤ የሰብኣዊ ኮሚሽን ቅማንትን የሚመለከት ሪፖርት፤ በቅማንትና በአማራ ህዝቦች መሀከል የተፈጠረው ችግር ህወሓትና የትግራይ ተወላጆች የፈጠሩት ነው፤ በእርግጥ አፍ አውጥተው እንደ መንግስቱ ሃይለማርያም ይህ ጠመኔ እንኳ መግዛት የማይችል ብለው አልተናገሩም ሁሉ የተናገሩት ግን ህወሓትና የትግራይ ተወላጅ ለማሸማቀቅና ከሌላው ህብረተሰብ ለመነጠል አስበው ራሱን ደፍቶ እንዲኖር የሰሩት ስለመሆኑ ልብዎ ያምናል ስለሆነም ማስመሰሉ ይቅርብዎት:: እንዳሉትም የወረደ ሞራል ቢኖርም የረባ ምክንያት ግን የለዎትም::

አሁን ደግሞ ሁሉም የትግራይ ተወላጅ አለበት የሚሉ ቦታ ጨርሰው የመከላከያ ሰራዊት 95% ጀነራል መኮነን የትግራይ ተወላጅ ነው ይሉናል ከ93 ዓ/ም ጀምረው የያዙት ተመሳሳይ ጩኸት በመሆኑ አዲስ ነገር ባይሆንም እስኪ ማን ይሙት በዚህች አገር ይህን ያህል የአንድ ብሄር የበላይነት ያለው ይህን የመሰለ ከጫፍ እስከ ጫፍ በሁሉም ብሄር ብሄረ ሰቦች አለፎም በጎረቤት አገራት ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ህዝባዊ ሰራዊት መገንባት ይቻላል? ህወሓትና ኢህአደግ አለፍ ሲልም የትግራይና የአማራ ህዝቦች ይህን አያምኑም:: ይህች ለቅሶ ከፍየል ሞት በላይ ናት እንደተባለው ለወደፊት መገንባት የምትፈልጉት ሰራዊት እየነገሩን እንደሆነ አያጠያይቅም::

በተረፈ ግን እባክዎ ሞራሉና ስብእናው ካልዎት ባለፈው ፅሁፎ የተቀስኳቸውና አድበስብሰው ያለፋዋቸው ጉዳዮች ደግሜ ላስታውስዎትና ተገቢ ማብራርያና ምላሽ ቢሰጡ፤

1. በሽግግር ወቅት ኢህአፓ ተጋብዘዋል ብየ ነበር ለምን መዋሸት እንደፈለጉ ቢነግሩን፤ ደግሞ ጥያቄው ከደርግ ውድቀት በኋላ እንጂ ከዛ በፊት ኢሰፓ የሚካፈልበት የሽግግር እንዲመሰረት ኢህአደግ በሎንደን ድርድር እንዳቀረበ አውቃለሁ
2. ህወሓት ጠባብና ዘረኛ አመለካከቱን የበላይነት ለመፍጠር ብዙ ሰርተዋል ብለው የቅማንት ችግርና የስድስተኛ ክፍል ችግር እንዲፈጥር አድርገዋል ብለዋል ማስረጃ አለዎት
3. ብአዴን በጥልቅ ተሃድሶ መፍታት ነበረበት ብየ ያስቀመጥኳቸው አራት ነጥቦች ያለዎትን ሃሳብ ያካፍሉን እንደተለመደውና አብረን ለመጓዝ ስለሚያስችሉን

እነዚህንና ሌሎችም የተጠቀሱ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አተኩረው ቢያብራሩ የብስለትዎና የሞራልዎ መለኪያ ይሆናሉ አለበለዚያ በሌሎች ሰዎች ላይ የሚሰነዘረው ትችት (ቀደም ብለው የአቶ ገዱ አሁን ደግሞ የአቶ ሲሳይ)መልስ የመስጠትና ጠበቃ መሆን አሽከርነት (Foot Soldier) እንጂ ስብእናዎና ሞራልዎ አያሳይም::